# ለማስተዋወቅ ያህል . . .

ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ላቀች ብርሃነ ጋር የትዳር ሕይወት የጀመሩበትን ሃምሳ ሰባተኛ ዓመት (አዎ፥ ፺፯!) የጋብቻ በዓላቸውን ያከበሩት ከአራት ወራት በፊት ባለፈው የታኅሣስ ወር ነበር። ለሚያያቸው ሰው እኒህ የዕድሜ ባለጸጋ የ፹፯ ዓመት አዛውንት አይመስሉም። በጣም ቀልጣፋና ቆፍጣና ኢትዮጵያዊ ናቸው። ሲቆሙም ፥ ሲቀመጡም፥ ሲራመዱም እንደጥሩ ስፖርተኛ በጣም ንቁ ናቸው። በማይጨው ጦርነት ወራሪውን የኢጣሊያን ጦር ከመሰል አርበኞች ጋር የተጋፈጡ፥ «ፋኖ» ብለው በዱር በገደል የተንከራተቱ፥ ለዛሬው ትውልድ ባለውለታ የሆኑ ሰው ናቸው። በአርበኝነት ያሳለፏቸው ዓመታት የጀግንነት ባሕርይ ስላላበሷቸው ሳይሆን አይቀርም፤ ዛሬም ከፍተኛ አካላዊና አእምሮአዊም ንቃት የሚታይባቸው። በተረጋጋ አንደበት የሕይወት ልምዳቸውን ሲተርኩ ከጣፋጭ የአተራረክ ስልታቸው ባሻገር ጥቃቅን ነገሮችን የማስታወስ ችሎታቸው ሰሚውን ማስገረሙ አይቀርም። አገራዊና ወገናዊ የአርበኝነት ግዴታቸውን ከተወጡ በኋላም በተለያየ መስክ አገራቸውን አገልግለዋል። በተለይም የመድረክ ሰው ሆነው አዲስ አበባ በሚገኙት የማዘጋጃ ቤትና የብሔራዊ ቴአትር ቤቶች ከሰላሣ በላይ ተውኔቶች ውስጥ በተዋናይነት ተሳትፈዋል። ለአብነት ያህል በብሔራዊ ቴአትር የደጃዝማች ግርማቸው ተክለሃዋርያትን ድርሰት ተመርኩዞ በተቀነባበረው «ቴዎድሮስ» ቴአትር ውስጥ አፄ ቴዎድሮስን፤ እንዲሁም «አልሞ ትኩም ብዬ አልዋሽም» በሚል ርዕስ በቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው በተደረሰው ተውኔት ውስጥ የአቶ ተማቹን ገጸባሕርይ በመሪ ተዋናይነት ሠርተው በሕዝብ ዘንድ አድናቆትንና ተወዳጅነትን አትርፈዋል —አቶ መኰንን አበበ።

በዚህ በያዝነው የ፲፱፻፺፱ ዓመተ ምሕረት ፷፮ኛውን የሚያዝያ ፳፯ን የድል ቀን እናስባለን። ቀጥሎ የምታነቡት አጭር ታሪክ ከአቶ መኰንን እይታ አንፃር ማይጨውን ይቃኛል። በሕይወት ያሉ ሌሎች አርበኞች የየራሳቸውን የግል ልምድና አመለካከት ቢያካፍሉን የዛሬውንና መጪውንም ትውልድ ይጠቅማሉና ይህ የአቶ መኰንን ጽሑፍ ሌሎችን በራሳቸው አገላለጽ የጎደለውን ለማሟላት እንዲተጉ ይጋብዛቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ከተለያየ አቅጣጫ የሚሰበሰበው የዐይን ምስክርነት የዚያን ታሪካዊ ወቅት ሙሉ ስዕል ለማየት ይረዳናልና ታሪካቸውን ያልጻፉልን እንዲጽፉልን አደራ እንላለን። የእያንዳንዱ አርበኛ የግል ታሪክ ስለወቅቱ ያለንን ግንዛቤ ከማጎልበት በተጨማሪ የግለሰቡ ዜጋዊ፥ ስነልቡናዊና ማህበራዊ ስብእና ነጸብራቅ ስለሆነ ታሪካቸውን ሊጽፉ የሚፈልጉ የዐይን ምስክሮች ወይም ቤተሰቦቻቸው ሊበረታቱ ይገባቸዋል እንጂ «ተጽፎ ያለቀ ታሪክ ነው» ተብሎ ችላ ሊባሉ አይገባም። አቶ መኰንን አበበ በእጃቸው ጽፈው የሰጡኝን ቀጥሎ የምታነቡትን ማስታወሻ ታይፕ ከማድረግና ይህችን አጭር መግቢያ ከማዘጋጀት ውጪ ሌላ ያደረግሁት ነገር የለም፤ ጽሑፉ ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው የራሳቸው ነው። እኔ የጨመርኩት ወይም የቀነስኩት ቃል የለም።

የወራሪን ጦር ድል ለመምታትና አገርን፥ ነፃነትንና ክብርን ላለማስደፈር በተደረገ ታሪካዊ ትግል ውስጥ ተሳታፊ መሆን በአርበኛው ዐይን ሲታይ ምን ይመስላል? የአቶ መኰንን አበበ የማይጨው ጦርነት ትዝታ በአጭሩ፥ በራሳቸው ብዕር . . . እነሆ።

ቴዎድሮስ አበበ
ስፕሪንግፊልድ፥ ቨርጂኒያ
ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

# የማይጨው ትዝታዬ

## ከመኰንን አበበ

በዘመኑ አዲስ አበባ የክብር ዘበኛ ተብሎ ቁጥሩ አናሣም ቢሆን፤ የሚሰለጥን ሠራዊት ተቀጥሮ ለአንድ ወታደር ሁለት ብር ደመወዝ ይከፈለው ነበር። የቀረው ሕዝበ ሠራዊት ግን ከዳግማዊ አፄ ምኒልክ በተላለፈው ሥርዓት መሠረት ስንቁም፣ ልብሱም ከራሱ ከግለሰቡ የተሰናዳው ነው እንጂ ሌላ ተመንግሥት የሚሰጥ መሰናዶ፣ ስንቅና ልብስ አልነበረውም። ልብሱም የጦር ልብስ ካኪ ባለመሆኑ፣ አቡጀዲውን የቀንጠፋ፣ የአባሎ ዛፍ ቅርፊትና የመቅመቆ ሥር ተቀጥቅጦ ይነከራል፤ ነጭ ከመሆን ይልቅ ወደቢጫው ቀለም የመሰለ ሆኖ ይታያልማለት ነው።ስፌቱ ግን እጀጠባብና «ባትለሁለት» የተሰኘ አጭር ሱሪ ሆኖ ነበር የሚሰፋው። በዚህም የተነሣ ክብር ዘበኞችን «ኮት ለባሾች ይዝመቱ!» የሚል መጠነኛ የቅሬታ ማጉረምረም ድምጽ ለጊዜው ቢሰማም ያገር ጉዳይ ነበርና ከዳር እዳር ሁሉም ተነስቶ ተዘመተ። ንጉሠ ነገሥቱም ተክብር ዘበኞችና ከሕዝበ ሠራዊቱጋር ዘምተው በውጊያው ላይ አዋጊም ተዋጊም ሆነው እንደመተማው ዮሐንስ ለመሰዋት መሞታቸውን ሲመርጡ አብረዋቸው የነበሩት መኳንንትና እጨጌ ገብረጊዮርጊስ (በኋላ አቡነ ባስሊዎስ) «እዚህ ቢሞቱኮ ለራስዎ ታሪክ ማንጸባረቂያ ነው እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት አይጠቅምም፤ ስለዚህ በዓለም መንግሥታት ማሕበር ስለገቡ ሄደው የደረሰውን ግፍ ማስረዳት አለብዎት» ብለው መለሷቸው።

ከዚያም አዲስ አበባ መናገሻ ከተማ ተመልሰው በቅርብ ለተገኘው አድማጭእንዲህ ሲሉ ተናገሩ፤ «በዓለም መንግሥታት ማሕበር ተመዝግበን ማሕበርተኛ ስለሆን፣ በዘመቻው ላይ የደረሰውን ግፍና በደል፣ በዓለም በተከለከለው የመርዝ ጭስና ባይሮፕላን ቦንብ



በወቅቱ የነበረው የክብር ዘበኞች አለባበስ

ፎቶግራፍ ከአቶ መኰንን አበበ

በሰላማዊው ሕዝብና በቤተክርስቲያን ላይ ጥሎ ማቃጠሉንና ሰላማዊውን ሕዝብ መፍጀቱን እናሣውቃለን፤ እዚህ የምትገኙትም በዱር በገደል እየተዘዋወራችሁ ስትከራከሩ ቆዩን፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ እንመለሣለን» ሲሉ ሽንፈቱሕጋዊ ሽንፈት እንዳልሆነ ተናግረው በየግምጃ ቤቱ ያለውን የንኬልና ልዩ ልዩ ገንዘብ እንዲዘረፍ ፈቅደዋል ተብሎ በየባላገሩም የመንግሥት የእህል ጎተራ ሁሉ ተዘረፈ፤ እንዲሁም ቡልጋ ኮረማሽ የነበረው የጦር መሣሪያ ግምጃ ቤት ተዘርፎ በአርበኝነት ለተሰማራው አገር ወዳድ ሕዝብ የጠላት መከላከያ ሆነ። ጠላት ወደማህል አገር በመግባትና በአንዳንድ አመቺ ቦታ ምሽግ ተመመሸጉና መገናኛ መንገድ ለመሥራት ተመጀመሩ በፊት ተማይጨው ጦርነት በሕይወት የተመለሱት ዘማቾች ጣሊያን ሰላማዊውን ሕዝብ በአይሮፕላን ቦንብና በመርዝ ጭስ የፈጀ መሆኑን ያስረዳሉ። ድርጊቱ ራሱ ከመቀስቀሱም በላይ ንቃት ያላቸው የክብር ዘበኞችና ተከተማ ወደእየባላገሩ የወጡት ግለሰቦች በየፊናቸው ነፃነትን ማጣት ምን ያህል ችግር እንደሚያመጣ ሲያስረዱ ሕዝቡ ተቀባይ በመሆኑና በትምህርት የተገኘ ዕውቀት ሣይኖረው በተፈጥሮ ዕውቀቱና ባገር ወዳድነቱ ብቻ «ሞ ረሽ!!» እያለ በመጠራራትና ጥሪውን በመቀባበል፤

በምንጃርም በኩል፣ በሸንኮራ በኩል እሪታው ምንድነው?!!
በከሰም በቡልጋ እሪታው ምንድነው?
ባንኮበር በይፋት እሪታው ምንድነው?
በግድም በጅሩ፣ በመንዝ በተጉለት እሪታው ምንድነው?
በወሎ፣ በትግራይ ቅሬታው ምንድነው?
ዝምታው ምንድነው?
በመሬው በእንሣሮው እሪታው ምንድነው?
ዝምታው ምንድነው?
በዠማ ባታክልት እሪ በል ዝምታው ምንድነው?
በጐንደር በጎጃም እሪ በል ዝምታው ምንድነው?
በሐረርስ በኩል፣ በውጋዴን በኩል ዝምታው ምንድነው?
በባሌ፣ ባሩሲ ዝምታው ምንድነው?
በሲዳሞ ስ በኩል ዝምታው ምንድነው?
በኢልባቦርስ ዝምታው ምንድነው?
በጅማ፣ በወለጋም በኩል እሪ በል!!
ዝምታው ምንድነው?
ቅሬታው ምንድነው?
ሱሪን፣
ሱሪን ለሚያጠልቃት ወንድነት ዛሬ ነው
ጀግንነት ዛሬ ነው!

እየተባባለ፤ ገበሬው በሬውን እየሸጠ ጠብመንጃና ጥይት እየገዛ ሞ ፈሩን ሰቅሎ የጎበዝ አለቃ እየመረጠና በተመራጩ እየተሰባሰበ በየቦታው ተሰማርቶ ውጊያውን ቀጠለ። በፍቅረማርያም አባተጫን መሪነት አዲስ አበባ ተከቦና ቀበና ድረስ ተገብቶ ጠላትን አሸብሮት ነበር። ከዚያም ግራዝማች ቀኛዝማች እየተባለ ይሿሿም የነበረው በጠላት በኩል ቀለል ብሎ እንዳይታይ በማለት የልጅ ኢያሱን ልጅ መልዓከፀሐይ ኢያሱን ማንገሥ ለጠላት ክብደት ይሰጠዋል በሚል አስተሣሰብ ተመከረና መልዓከፀሐይ ኢያሱ ተአብዬ ገዳም ተፈልጎ ተወሰደና አነገሡት። መልዓከፀሐይ ኢያሱ ሲነግሥ ፍቅረማርያም አባተጫን አልነበሩም፤ ከጠላት ጋር ሲፋለሙ ሞ ተዋል። በምትካቸው ባላምባራስ አበበ አረጋይ በመልዓከፀሐይ ኢያሱ ራስ ተብለው ተሾሙ። ሌሎችም በየደረጃው ተሾሙ። የበፊቱም የእርስ በርስ ሹመት ፀደቀላቸው፣ ትግሉም ቀጠለ። መልዓከፀሐይ ኢያሱ ግን ወደፍቅሬ ግምብ ስንኳዝ ታሞ ስለነበር ባጭር ቀናት ውስጥ ሞ ተ። ትግሉ ግን ቀጠለ። ከዚያም በእንግሊዝ ረዳትነት በሱዳን በኩል የድሉ ሁኔታ እየገፋና እየተሰማ ሲመጣ፣ ጠላት

ለማባበል ሲል ብዙ ሹመት ሰጠ። ነጋድራስ ተሰማ እሸቴም ደጃዝማች ተብለው ተሾሙ፣ በተለመደ ቅኔያቸው

አያችሁልኝ ወይ የአምላክ ቸርነት፣ የእግዜር ቸርነት
ከተሰማ ወዲያ ደጃዝማችነት

ያሉትም በዚያን ጊዜ ነበር።

ከዚያም የእንግሊዝ አይሮፕላን በኢትዮጵያ ምድር አንጃበበ፣ ጠላትም ተደናገጠ። አርበኛውም ከቆላ ተበረሐው ወደእያቅራቢያው የጠላትን ምሽግ እያስለቀቀ መግባት ጀመረ። በምሥራቅ በኩል የመጣው ጦር ምንም ስላላጋጠመው ሰተት ብሎ ገብቶ በኢትዮጵያኖች ስደተኞችና በእንግሊዝ መኰንኖች መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. አዲስ አበባ ተያዘች፤ ባንዳውም፣ አርበኛውም የቆላውም የደጋውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ደስታ፣ ሆታ ሆነ። ራስ አበበ አረጋይም ተቡልጋ ደብረብርሃን ሲደርሱ፣ ወደሰሜን እነደጃዝማች ሀብተሥላሴ በላይነህን፣ እነደጃዝማች ከበደ ካሣን፣ እነደጃዝማች ኪዳኔ ወልደመድህንን፣ እነደጃዝማች ቁምላቸው ገብረ ወልድን ሌሎችንም ጠላትን ማለትም ጀነራል ናዚን ተከታተለው እንዲይዙ ወደ ጐንደር ልከው እሣቸው ግን የቀረነውን ሠራዊት አስከትለው በጅሩ፣ በሰላሌ፣ በሱሉልታ አዲስ አበባ እንጦጦ ራጉኤል ገባን። ጃንሆይም ተስደት መልስና ከጨረቃ ጦርነት ድል ለጥቆ፣ በኦሜድላ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቅለው ተውለብለቦ ነበርና ከዚያም በሶስተኛው ወር መሆኑ ነው በወጣው ፕሮግራም መሠረት በጎጃም አርበኞች ታጅበው ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. አዲስ አበባ ሲገቡ በታላቅ ሰልፍ አቀባበል ተደረገ፤ የጦር አለቆችም፣ አርበኞችም የጦርነት ሙያቸውን በፋከራ ገለጡ። የሹመት መጀመሪያ፣ ራስ አበበአረጋይ ወዲያው የአዲስ አበባ ጥብቅ ገዥ ሆነው ተሾሙ። እኛም በአምስት ሻምበል የምንመራ የአርበኞች ሠራዊት ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. የአዲስ አበባ ዙሪያ በሮችንና ታላላቅ ድርጅቶችን ተረክበን ፀጥታውንም ጭምር ለመጠበቅ ተደለደልን።



አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ በሚያዝያ ፳፯ የነፃነት ሐውልት አደባባይ የተነሣነው ምስል።

ፎቶግራፍ ከአቶ መኰንን አበበ